# OUR SCHOOL SYSTEM

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# 160,564 STUDENTS*

* ፎል 2020 መደበኛ ምዝገባ

# 208 SCHOOLS

**135** Elementary SCHOOLS **40** Middle SCHOOLS **25** High SCHOOLS

5 ልዩ (ስፔሻል) ትምህርት ቤቶች • 1 አልተርኔቲቭ ፕሮግራም •
2 የጨቅላ ህፃናት (ኤርሊ ቻይልድሁድ) ትምህርት ማዕከሎች

**ትልቁ ዲስትሪክት በሜሪላንድ** | **14th LARGEST school system in the UNITED STATES**

## 2019-2020 የተማሪዎች ስብጥር




## ምዝገባ

**+21,327**

2009: 139,237

እስከ ፎል 2020: 160,564

## አውቶቡሶች

**100,000 ማይሎች በቀን**

= ከአራት ጊዜ በላይ በኢኩዌተር ዙርያ

(1,307 አውቶቡሶች)

## 2019 MCPS የተመራቂዎች ብዛት:-

አጠቃላይ 88.7%




የ MCPS ተመራቂዎች ብዛት ከስቴት እና ከአገርአቀፍ አማካይ መጠን ከፍተኛ ነው።

## አገልግሎቶች

**25 ሚሊዮን**

ስኩዌር ጫማ የት/ቤትና ጽ/ቤት ቦታ ማጽዳት እና መንከባከብ

## የተሰጡ ስኮላርሽፖች

**$393 ሚሊዮን**

ለ 2019 ተማሪዎች

## አገልግሎትቶች 2019-2020

**11.7%** receive Special Education Services

**18.2%** participate in English for Speakers of Other Languages (ESOL)

**33.8%** participate in Free and Reduced-Price Meals (FARMS)

## የእኛ የሥራ ግብረኃይል

2019-2020

**24,029**

\# የሠራተኞች ብዛት

# ከሱፐርኢንተንደንቱ የቀረበ የሥራ ማስኬጃ ባጀት

## — የባጀት ዓመት 2022 / ዲሰምበር 2020 —

## አጭር መግለጫ

ለባጀት ዓመት 2022 የቀረበው የሥራ ማስኬጃ ባጀት ስለ ተማሪዎች፣ መማሪያ ክፍሎች እና ለትምህርት ቤቶች ያለንን ትኩረት የሚያስቀጥለን ይሆናል። ይህ ባጀት የዋነኛ ዓላማችን ትኩረት ተማሪዎችን በሙሉ ስለወደፊት ህይወታቸው መለምለም፣ ማደግ፣ መበልፀግ ጓግተው እንዲሠሩ በማዘጋጀት ረገድ ማእ ከላዊ ድርሻ ይኖረዋል። በተመሣሣይ ሁኔታ፥ ይህ ባጀት የተዘጋጀው በኮሮናቫይረስ ሳርስ-ኮቭ-2 ወረርሽኝ "coronavirus SARS-CoV-2 (COVID-19 pandemic)" ወቅት በመሆኑ በአገራችን፣ በስቴት እና በካውንቲ፣ እንዲሁም በዲስትሪክታችን የመማር ማስተማር ተግባር ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ይታ ወቃል።

## ⬇ ሜይንተነንስ ኦቭ ኤፈርት ፈንድ (MOE) ተቀንሷል

ወረርሽኙ ባስከተለው ተጽእኖ ምክንያት፥ ሰፕተምበር 30/2020 በ MCPS ከምዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል መደበኛ ምዝገባ ብቃት ያላቸው የሙሉ ጊዜ ተማሪዎች (FTE) ባለፈው ዓመት ተመሣሣይ ጊዜ ከተመዘገቡት በ 3,641 የተማሪዎች ቁጥር ያነሰ ነው። ይህም አሁን ባለው የ MOE ህግ መሠረት፥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ለባጀት ዓመት 2022 ማዋጣት ያለበትን የአካባቢ አስተዋጽኦ ገቢ በ $39,769,806 ይቀንሳል።

### ወጪዎች

| | |
|---|---|
| የ 2021 በጀት | $2.76 ቢልዮን |
| የባጀት ዓመት 2022 በጀት | $2.71 ቢልዮን |
| ለውጥ | ($42.6) ሚሊዮን |
| መቶኛ/ፐርሰንት | -1.5% |

## ሌሎች የባጀት ነክ ስጋቶች

- ⬇ ከሜሪላንድ ስቴት እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ይደረግ ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ የባጀት ቅነሳ
- ⬇ የሜሪላንድ የትምህርት/ኪርዊን ፈንድ ብሉፕሪንት ማስወገድ (Termination of the Maryland Blueprint for Education/Kirwin Funding)
- ⬆ በድህረ ወረርሽኝ ምዝገባ የሚመለሱት—2,500-3,000 ተማሪዎች እንደሚሆኑ ይገመታል
- ⬆ የድህረ ወረርሽኝ የጤና እንክብካቤ ወጪዎች ለህክምና ሒደቶች መዘግየት ምክንያት ሊሆን ይችላል

| | |
|---|---|
| ተመላሽ ተመዝጋቢዎች | $8,908,332 |
| አዲስ ቦታ | $1,146,319 |
| ግሽበት | $443,836 |
| የለውጡ መጠን/ሌላ | $1,463,866 |
| የተመደበ ባጀት/ ኢንተርፕራይዞች/ሌላ | ($28,136,495) |
| ገንዘብ ያለመባከን እና ቅንስናሾች | ($26,422,007) |
| **ጠቅላላ የባጀት ለውጥ** | **($42,596,149)** |

## አስፈላጊ ኢንቨስትመንቶች/እሳቤዎች

- ✓ ወደ MCPS ለሚመለሱ ተማሪዎች ሠራተኞችን ማሟላት
- ✓ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች የአእምሮ ጤንነት/የማህበራዊ-ስሜት ድጋፎች
- ✓ የባከኑ የትምህርት ጊዜያትን ለማካካስ እና የሚያታግላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ተጨማሪ የትምህርት ድጋፎችን መስጠት
- ✓ ለቀጣይ ቨርቹወል ትምህርት እና ቴክኖሎጂ እንደአግባብነቱ ድጋፍ መስጠት

## የማህበረሰባችን የልብ ትኩረት

በማናቸውም ዓመት እጅግ በጣም አስፈላጊ ኢንቨስትመንት የነበረው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞችን መደገፍ ነው። መምህ ራን እና የመምህራን መሪዎች አካደሚያዊ ፕሮግራሞችን በቨርቹወል ሽግግር ለመምራት ችለዋል ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችም ለቤተሰቦች ቁሳቁሶችን እና አገል ግሎቶችን በመስጠት ረገድ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎችን በመጠቀም ውጤታማ ሥራዎችን አከናውነዋል። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት፥ የ MCPS ሠራተኞች በሙሉ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ከከሪኩለም ባሻገር የሚከናወኑ ተግባሮችን (አክቲቪቲዎች) እና ስፔሻል ፕሮግራሞችን ዳግም የመተለም ሥራዎችን አከናውነ ዋል። የማህበረሰባችን የልብ ትርታ እንደመሆናቸው መጠን ጥራት ያላቸው ሠራተኞችን እስከወዲያኛው መጠበቅና ማቆየት ወሳኝነት አለው።

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*